የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

**መመሪያ ቁጥር 22/2016**

**የምክር ቤት አባላት በመራጮቻቸው አመኔታ በሚያጡበት ጊዜ ስለሚወሰድ እርምጃ ዝርዝር የአሰራር ስርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ**

በምክር ቤት አባል የስነ-ምግባር ብልሹነት ምክንያት ምክር ቤቱ የሚወስደው እርምጃን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 88/1989 አንቀጽ 6 መሰረት በግልፅ መደንገጉ እንደተጠበቀ ሆኖ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 12 (3) ህዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ለማንሳት እንደሚችል እንደ አንድ የህገ መንግስቱ መርህ የተቀመጠ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት በአንቀጽ 54(7) ማናቸውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በህግ መሰረት ከምክር ቤት አባልነት ሊወገድ እንደሚችል ስለሚደነግግ፤

ህዝብ በተወካዩ ላይ አመኔታ በአጣበት ጊዜ የመራጩ ህዝብ ጥያቄ የማስተናገድ ኃላፊነቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በመሆኑ፤ ጥያቄው ሲቀርብ የሚስተናገድበትን የአሰራር ስርዓት መደንገግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ይህ መመሪያ እንዲወጣ ሆኗል።

**ምዕራፍ አንድ**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

**አንቀጽ 1. <u>አውጪው ባለሥልጣን</u>**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7/11/ እንዲሁም የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 163/2/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት እንዲሁም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በመራጮቻቸው አመኔታ በሚያጡበት ጊዜ ስለሚወሰድ እርምጃ በወጣው አዋጅ ቁጥር 88/1989 አንቀፅ 4 ንዑስ ቁጥር 1 እና 3 በተገለፀው መሠረት ይህን መመሪያ አዉጥቷል።

**አንቀጽ 2. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ ***"የምክር ቤት አባላት* በመራጮቻቸው አመኔታ በሚያጡበት ጊዜ ስለሚወሰድ እርምጃ ዝርዝር የአሰራር ስርዓት*ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 22/2016* "**ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 3. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1) **"የይውረድልን ምርጫ"** ማለት በምርጫ ክልሉ የሚገኙ መራጮች ያቀረቡት የይውረድልን ማመልከቻ በቦርዱ ተቀባይነት ካገኘ የይውረድልን ጥያቄው ላይ መራጩ ህዝብ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚከናወን ምርጫ ነው።
2) **"የምርጫ ክልል"** ማለት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል በምርጫ ያሸነፈበት የምርጫ ክልል ማለት ነው፤
3) **"ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 ስልጣንና ተግባሩ እንደገና የተወሰነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።
4) **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው።
5) **"የምርጫ ጽ/ቤት"** ማለት የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ምርጫ ያሸነፈበት የምርጫ ክልል ላይ ቦርዱ ያቋቋመው የምርጫ ጽ/ቤት ማለት ነው።
6) **"የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢ/ዎች"** ማለት የምርጫ ክልሉን ህዝብ በመወከል የአንድ ምክር ቤት አባል ከምክር ቤት አባልነቱ እንዲነሳ የመጀመሪያ ማመልከቻ እንደአግባብነቱ ለቦርዱ ዋና ጽ/ቤት፣ ለክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ለምርጫ ክልል ጽ/ቤት የሚያቀርብ/ የሚያቀርቡ፤ ተወካዩን ለመምረጥ በምርጫ ክልሉ ምርጫ ሲደረግ ተመዝጋቢ የነበሩ የምርጫ ክልሉ መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ ከምክር ቤት አባልነት ይውረድልን የሚለውን ጥያቄ ተፈፃሚ ለማድረግ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት የሚከናወኑ ተግባራትን በራሳቸው ወይም ከመካከላቸው በሚመርጧቸው ወኪሎች አማካይነት የሚያከናውኑ ሰዎች ናቸው።
7) የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ላይ የተካተቱ የቃላት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡

**አንቀጽ 4. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በፌዴራል የህዝብ ተወካዮች እና በክልል ምክር ቤቶች መራጩን ህዝብ እንዲወክሉ በተመረጡ የምክር ቤት አባላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

**አንቀጽ 5.** **<u>የጾታ አገላለጽ</u>**

በዚህ መመሪያ በአንደኛው ጾታ የተገለጸው ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል፡፡

**አንቀጽ 6.** **<u>አላማ</u>**

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ህዝብ በመረጠው የምክር ቤት አባል ላይ አመኔታ በሚያጣና የይውረድልኝ ጥያቄ በሚያቀርብ ጊዜ ሂደቱን የሚያስፈጽሙ አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀትና ዝርዝር የአፈፃፀም ሥርዓት በመደንገግ አመኔታ በማጣት ምክንያት የሚቀርብን የይውረድልን ጥያቄ ግልፅ፣ አሳታፊ እና ተአማኒ በሆነ መንገድ መከናወኑን ማረጋገጥ፤
2. የቀረበው ጥያቄ በእርግጥም የመራጩ ህዝብ ጥያቄ መሆኑን በሚገባ ማረጋገጥ የሚቻልበትን ግልፅና ውጤታማ የሆነ ስርዓት መዘርጋት፤
3. የይውረድልን ጥያቄውን በመጀመሪያ ያቀረቡት አቅራቢዎች የህዝብ ድጋፍ መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በሚገባ በመፈፀም መራጩ ህዝብ በእርግጥም ጥያቄውን ያቀረበ መሆኑን የሚያረጋግጡበትን ተግባራት ያለማናቸውም አካል አሉታዊ ተፅእኖ ለማከናወን የሚችሉበትን ስርዓት መዘርጋት፤
4. ጥያቄውን ያቀረቡትና በይውረድልን ጥያቄው ላይ የህዝብን ውሳኔ ለማረጋገጥ በሚደረገው ምርጫ ለመሳተፍ ብቁ የሆኑ በምርጫ ክልሉ የሚገኙ መራጮች ያለ ምንም አድሎ እና ያልተገባ ጫና በድምጽ ሰጪነት በመሳተፍ ውሳኔያቸውን የሚያሳውቁበት ግልጽ፥ አሳታፊ እና ተአማኒ አሰራር መዘርጋት፤
5. የይውረድልን ጥያቄ አቀራረብ ስርዓቱን እና በዚሁ መነሻነት የሚከናወነው ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ፣ ቆጠራ እና የውጤት አገላለጽ ሂደት ግልጽ ፣ ቀልጣፋ፣ በአለም አቀፍ እና በሀገሪቱ ህጎች ላይ የተደነገጉ መመዘኛዎችን ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ ፤

**ምዕራፍ ሁለት**

**<u>በይውረድልን ጥያቄ የቦርዱ እና የማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች ተግባርና ኃላፊነቶች</u>**

**አንቀጽ 7.** **<u>የቦርዱ ተግባር እና ኃላፊነት</u>**

1. መራጩ ህዝብ ያቀረበውን የይውረድልን ጥያቄ በሚገባ ተፈፃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ብቃት ያላቸው አስፈጻሚዎችን ጥያቄ በቀረበበት የምርጫ ክልል ያሰማራል በምርጫ ክልሉ በመደበኛነት እንዲያገለግል የተቋቋመ ምርጫ ፅ/ቤት ከሌለ የምርጫ ፅ/ቤት ያዋቅራል::

2. የይውረድልን ጥያቄውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሰነድና ቁሳቁሶችን በበቂ ሁኔታ ያዘጋጃል፤ በጥንቃቄ እና በወቅቱ ጥያቄ የተነሳበት ምርጫ ክልል እንዲደርሱ ያደርጋል።

3. በቦርዱ ተቀባይነት ያገኘ የይውረድልን ጥያቄ መሰረት የሚደረግ የይውረድልኝ ምርጫ የሚከናወንበትን የጊዜ ሰሌዳ ጥያቄውን ካቀረቡ መራጮች፣ ተወካዮች እና ጥያቄ ከቀረበበት የምክር ቤት አባል እና ሌሎች የምርጫ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ያዘጋጃል።ጥያቄ በተነሳበት ምርጫ ክልል ለሚኖረው ህዝብ ይፋ ያደርጋል።

4. የይውረድልን ጥያቄው በቦርዱ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ የሚደረገው የይውረድልኝ ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ ሂደት የምርጫ ህጉ እና ቦርዱ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት በሰላማዊነት፣ ፍትሃዊነት፣ በእውነተኝነት፣ ያለአድልዎ እና በግልጽ መፈጸሙን ያረጋግጣል።

5. የይውረድልን ጥያቄውን ለሚያስፈፅሙ የቦርዱ አስፈጻሚዎችና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ባለድርሻ አካላት አስፈላጊው ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል።

6. ከይውረድልን ጥያቄው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት እንዲሁም ለምርጫ ክልሉ መራጭ ህዝብ በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል።

7. የይውረድልን ጥያቄው በቦርዱ ተቀባይነት አግኝቶ የይውረድልኝ ምርጫ የሚከናወንበትንና ምርጫ ጣቢያ የሚቋቋምባቸው ቦታዎችን በመለየት እና ቀኑን በመወሰነን ለምርጫ ክልሉ መራጭ በይፋ ያሳውቃል።

8. የይውረድልን ምርጫን ለመታዘብ ፍላጎት ላሳዩ የአገር ውስጥ ታዛቢዎች ወይም ዘገባ ለመስራት ለሚፈልጉ ጋዜጠኞች አግባብነት ባለው ህግና መመሪያ መሰረት ፍቃድ ይሰጣል።

9. የይውረድልን ምርጫ ውጤት ማረጋገጥና ይፋ የማድረግ ተግባር ያከናውናል።

10. በይውረድልን ምርጫ ሂደት ለሚቀርቡ ቅሬታዎች አስተዳዳራዊ መፍትሄ ይሰጣል።

11. በቦርዱ ወጥተው በስራ ላይ የሚገኙ መመሪያዎች እንደአግባብነታቸው በዚህ መመሪያ ላይ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

**አንቀጽ 8. የይውረድልን ጥያቄ ማስፈፀሚያ አደረጃጀቶች**

የይውረድልን ጥያቄ ተግባራዊ ማድረግ በሚያስፈልግበት ጊዜ ቦርዱ የሚከተሉትን ጽህፈት ቤቶች ያደራጃል፡-

1. ጥያቄ በቀረበበት የምርጫ ክልል ጊዜያዊ የምርጫ ፅ/ቤት ከሌለና አፈፃፀሙም በምርጫ ክልል ፅ/ቤት ተፈፃሚ መሆን አለበት ብሎ ቦርዱ ከወሰነ የይውረድልን ጥያቄውን የሚያስፈፅም የምርጫ ፅ/ቤት እንዲቋቋም ይደረጋል።
2. ቁጥሩ የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል በተመረጠበት ምርጫ ተመዝጋቢ የነበሩ መራጮችን ቁጥር መሰረት የሚያደርግ ሆኖ የይውረድልን ምርጫ የሚፈፀምባቸው ምርጫ ጣቢያዎች ያቋቁማል።

**አንቀጽ 9. የይውረድልን ጥያቄ አስፈፃሚዎች**

1. ቦርዱ አፈፃፀሙም በምርጫ ክልል ፅ/ቤት ተፈፃሚ መሆን አለበት ብሎ ከወሰነ የምርጫ ፅ/ቤት እንዲሁም በምርጫ ጣቢያ ደረጃ የይውረድልን ጥያቄውን እና ምርጫውን በገለልተኛነት እና በታማኝነት የሚያስፈጽሙ አስፈፃሚዎችን እንደየሁኔታው ጥያቄውን ያቀረቡት መራጮች ከሚገኙበት ምርጫ ክልል ውጪ ከሚኖሩ ነዋሪዎች መካከል ይመለምላል። በዚህም መሰረት አስፈጻሚዎቹ ፡-
   - ኢትዮጵያዊ የሆነች/ነ፣
   - ዕድሜው/ዋ 21 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነች/የሆነ
   - የፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነች/ ያልሆነ
   - የይውረድልን ጥያቄውን እና ምርጫውን ለማስፈፀም የሚሰጠውን ስልጠና በሚገባ ለመረዳት እና በዚህ መመሪያ መሰረት ለመፈጸም የሚያስችል የትምህርት ዝግጅት ያለው/ያላት፤
2. አስፈፃሚዎች ተግባራቸውን በብቃት እና በታማኝነት መወጣታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል በቦርዱ በተዘጋጀ የቃለ መሀላ ሰነድ ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል።
3. በንዑስ ቁጥር 2 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የምርጫ አስፈፃሚዎችን አሰራር እና ስነምግባር ደንብ ለመደንገግ የወጣው መመሪያ የይውረድልን ምርጫ እንዲያስፈፅሙ በምርጫ ክልል ፅ/ቤት እና በምርጫ ጣቢያዎች በተመደቡ ምርጫ አስፈፃሚዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

**አንቀጽ 10. የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት**

1. የምክር ቤት አባል ከምክር ቤት አባልነት እንዲነሳ የሚቀርበውን የመጀመሪያ ማመልከቻ እንደአግባብነቱ ይቀበላል።

2. በአንቀጽ 12(5) መሰረት አመልካቾች ያቀረቡትን የይውረድልን ማመልከቻ በመመርመር የተጓደለውን እንዲያሟሉ ያደርጋል፡፡
3. የቀረበው የይውረድልን ማመልከቻ በአንቀጽ 12(5)(ለ) መሰረት የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊው ፊርማ በማረጋገጥ ለቦርዱ ዋና ጽ/ቤት ማመልከቻውን ይልካል፡፡
4. የይውረድልን ማመልከቻው በምክር ቤቱ የመጀመሪያ አመት ወይም በመጨረሻ አመት የቀረበለት ከሆነ ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡
5. የቀረበው የይውረድልን ጥያቄ በበቂና አሳማኝ ምክንያት ተቀባይነት የሌለው መሆኑ በቦርዱ ሲታመን የቦርዱን ውሳኔ በአንቀጽ 13(3) መሰረት ለይውረድልን ማመመልከቻ አቅራቢዎች ያሳውቃል፡፡
6. ቦርዱ በሚሰጠው የስራ መመሪያ መሰረት ከምርጫ ክልል ጽ/ቤት ጋር በመተባበር የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

**አንቀጽ 11. <u>የምርጫ ክልል ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የምርጫ ክልል ጽ/ቤት የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የይውረድልን ጥያቄውን ዝርዝር አፈጻጸም በዚህ መመሪያ ላይ በተደነገገው መሰረት በዋነኛነት ይመራል፡፡
2. በይውረድልን ጥያቄው መነሻነት ለሚደረግ የይውረድልን ምርጫ በቦርዱ ቁጥራቸው ተለይተው እንዲቋቋሙ የተወሰኑት የምርጫ ጣቢያዎች መቋቋማቸውን እና በአግባቡ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፡፡
3. ቦርዱ በሚሰጠው የውሳኔ አግባብ መሰረት የምርጫ አስፈጻሚዎችን በመደልደል የይውረድልን ምርጫው ወደሚደረግበት ምርጫ ጣቢያ ያሰማራል፡፡
4. የይውረድልን ምርጫውን ለማስፈፀም ለተቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች በቦርዱ መመሪያዎች መሰረት መመሪያ ይሰጣል፣ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡
5. ለፅ/ቤቱ ከቦርዱ የሚላኩ የይውረድልን ምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ወደየምርጫ ጣቢያው ያሰራጫል፣ መድረሳቸውን ይከታተላል፡፡
6. ቦርዱ የሚያስተላልፋቸውን የስራ መመሪያዎች ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣ ለቦርዱም ተገቢውን ሪፖርትና መረጃ ያቀርባል፡፡
7. አስፈላጊ ሲሆን በቦርዱ እውቅና በይውረድልን ጥያቄው ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ያደርጋል፣ ይፋዊ መረጃ ይሰጣል፡፡

8. የይውረድልን ምርጫ ከተከናወነባቸው ምርጫ ጣቢያዎች የተላከለትን የመራጭ ድምጽ በመመሪያው መሰረት በማዳመር ለቦርዱ ይልካል።
9. በይውረድልን ጥያቄው መነሻነት የተደረገውን የይውረድልን ምርጫ የሚመለከት አጠቃላይ የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል።
10. ከቦርዱ ዋና ፅ/ቤት የሚሰጡ ሌሎች ለይውረድልን ሂደቱ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናል።

**አንቀጽ 12. <u>የምርጫ ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የይውረድልን ምርጫ በሚከሄድባቸው ጣቢያዎች የሚመደቡ አስፈፃሚዎች ተግባርና ኃላፊነቶች የሚከተሉት ናቸው::

1. ከቦርዱ የተላኩ የይውረድልን ምርጫ ማስፈፀሚያ ሰነድና ቁሳቁሶችን ተረክቦ በጥንቃቄ እንዲጠበቁ ያደርጋል።
2. በይውረድልን ምርጫ ለመሳተፍ መስፈርቱን የሚያሟሉ ድምጽ ሰጪዎች የሚያቀርቡትን በአዋጁ አንቀጽ 21 ከተመለከቱት መካከል ያለውን የማንነት ማረጋገጫ ሰነድ ከመራጮች መዝገብ ጋር በማመሳከር በድምፅ መስጫ እለት ድምፅ እንዲሰጡ ያደርጋል።
3. በድምጽ መስጫ ቀን ድምፅ ሰጪው ድምፅ ከመስጠቱ በፊት ስለድምጽ አሰጣጡ ገለጻ ይሰጣል።
4. ከጸጥታ አስከባሪዎች ጋር በመመካከር የድምፅ መስጫ ጣቢያው ሥነ-ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል።
5. ድምፅ መስጠቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቆጠራው በአግባቡ እንዲከናወን ያደርጋል።
6. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በቦርዱ መመሪያ መሰረት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ያደራጃል።
7. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የምርጫ ጣቢያውን የይውረድልን ምርጫ አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤ ለምርጫ ክልል ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል።
8. የይውረድልን ምርጫውን በሚመለከት ከምርጫ ክልል ፅ/ቤት የሚሰጡትን ሌሎች አግባብበት ያላቸውን ተግባራት ያከናውናል።

## ምዕራፍ ሶስት

## የይውረድልን ጥያቄ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት

### አንቀፅ 13. የይውረድልን ጥያቄ አቀራረብ

1. የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል በተወዳደረበት ምርጫ ክልል በመራጮነት ተመዝግበው የመረጡ 100 መራጮች የምክር ቤት አባሉ ከአባልነቱ እንዲነሳ በመጠየቅ የተፈራረሙበትን ማመልከቻ እንዳግባብነቱ ለቦርዱ ዋና ፅ/ቤት ወይም ለክልል ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ያቀርባሉ።
2. ማመልከቻው አመልካቾቹ የይነሳልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ቀደም ሲል በተወዳደረበት ምርጫ ክልል መራጭ የነበሩ መሆናቸውንና መርጠው የነበሩበትን ምርጫ ጣቢያ በሚገባ ለይቶ ማመልከት አለበት።
3. ማመልከቻ አቅራቢዎቹ በማመልከቻቸው ላይ የምክር ቤት አባሉ መነሳት አለበት ለማለት ያበቃቸውን ምክንያት መግለፅ ይኖርባቸዋል።
4. ከማመልከቻው ጋር የይውረድልን ጥያቄውን በሚመለከት አቅራቢዎቹን በመወከል ጉዳዩን እንዳግባብነቱ በክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲሁም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ በቦርዱ ዋና ጽ/ቤት በመቅረብ የሚከታተሉ ወኪሎች በማመልከቻ አቅራቢዎቹ የተወከሉበት ሰነድ ተያይዞ መቅረብ አለበት።
5. የቦርዱ ዋና ጽ/ቤት ወይም የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከላይ በተመለከቱት የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፆች መሰረት የተቀበለውን ማመልከቻ

    ሀ/ ያልተሟላ ከሆነ አለመሟላቱን እና መስተካከል የሚገባውን ጉዳይ ከሚያብራራ መግለጫ ጋር ማመልከቻውን ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥ ለወኪሎቹ በመመለስ የተጓደለውን ያሟላ ማመልከቻ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርቡ ያደርጋል።

    ለ/ የተሟላ ከሆነ ወይም የተጓደለውን እንዲያሟሉ የተጠየቁት ወኪሎች ድጋሚ ያቀረቡት ማመልከቻ በሚገባ መሟላቱን አረጋግጦ ቦርዱ ለዚሁ ጉዳይ በሚያዘጋጀው እና ለጽ/ቤቱ በሚልከው ቅፅ ላይ እንደአግባብነቱ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሀላፊው በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ በማድረግ ማመልከቻው በቀረበ በ5 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ዋና መስሪያ ቤት እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

    ሐ/ ማመልከቻ አቅራቢዎች የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኙ እንደሆነ ይግባኛቸውን ውሳኔው በደረሳቸው በ10 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ዋና ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላሉ።

**አንቀፅ 14. <u>የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት</u>**

1. የቦርዱ ዋና ጽ/ቤት ማመልከቻውን መርምሮ የቀረበው ጥያቄ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ተፈፃሚ ስለመደረግ አለመደረጉ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ውሳኔ በ15 ቀናት ውስጥ ይሰጣል። በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንደአስፈላጊነቱ ጥያቄ ያቀረቡ መራጮች ተወካዮች ተሳታፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።
2. ቦርዱ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል በቀረበው ማመልከቻ ላይ ያለውን አስተያየት እንዲያቀርብ ያደርጋል።
3. ቦርዱ የቀረበውን ጥያቄ በበቂና አሳማኝ ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ነው ብሎ ካመነ ውሳኔውን በራሱ ወይም እንደአግባብነቱ ለክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመላክ ጽ/ቤቶቹ የቦርዱን ውሳኔ ለይውረድልን ማመልከቻ አቅራቢዎቹ እንዲያሳውቁ ያደርጋል። በተጨማሪም የምርጫ ክልሉ ህዝብ ውሳኔውን በይፋ እንዲያውቀው ያደርጋል።
4. ማመልከቻ አቅራቢዎቹ በንዑስ ቁጥር 3መሰረት ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካላቸው ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።
5. ቦርዱ በቀረበው የይውረድልን ማመልከቻ መሰረት ጥያቄው ተፈፃሚ መሆን አለበት ብሎ ከወሰነ በቦርዱ ተዘጋጅቶ የሚላከውን የተመዘገቡ መራጮችን ማስፈረሚያ ቅፅ የይውረድልን ማመልከቻ ላቀረቡት አመልካቾች እንዳግባብነቱ ቦርዱ በሚያሰማራቸው የምርጫ አስፈፃሚዎች ወይም በሚያቋቁመው የምርጫ ፅ/ቤት አማካይነት እንዲደርሳቸው ያደርጋል።
6. ቦርዱ ያሰማራቸው ምርጫ አስፈፃሚዎች ወይም የምርጫ ፅ/ቤቱ ቅፁን በሚያስረክቡበት ሂደት የይውረድልኝ ጥያቄ አቅራቢዎቹ ወኪሎች የወሰዱበትን ቀን ያካተተ ማስፈረሚያ ላይ ፊርማቸውን እንዲያኖሩ ያደርጋሉ። የቅፁን ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀንም ይገልፁላቸዋል።

**አንቀፅ 15. <u>የተፈረመበትን ቅፅ የማቅረቢያ ጊዜ</u>**

1. ቦርዱ ከዋና ፅ/ቤት ካሰማራቸው አስፈፃሚዎች ወይም ከምርጫ ፅ/ቤት የመራጮችን ፊርማ ለማሰባሰብ የወሰዱት የይውረድልን ጥያቄ አመልካቾች/ወኪሎች በምርጫ ክልሉ የተመዘገቡ ከ15000/ አስራ አምስት ሺ/ በላይ መራጮችን በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ አስፈርመው የተፈረመበትን ቅፅ ከዋና ፅ/ቤት ለተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም ለምርጫ ፅ/ቤቱ እንዲያቀርቡ ይደረጋል። ቦርዱ የሚቀበለው አስገዳጅ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተፈረመበትን ቅፅ ማቅረብ ካልቻሉ ጥያቄውን እንደተዉት ይቆጠራል

2. የተፈረመበትን ቅፅ የማቅረቢያ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው አመልካቾቹ ከዋና ፅ/ቤት ለተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም ከምርጫ ፅ/ቤቱ የማስፈረሚያ ቅፁን ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ ነው።
3. የይውረድልን ማመልከቻ ያቀረቡት አመልካቾች ከቦርዱ በተሰጣቸው ቅፅ ላይ በምርጫ ክልሉ ከመረጡ 15000/ አስራ አምስት ሺ/ በላይ መራጮችን አስፈርመው እንዳቀረቡ ከዋና ፅ/ቤት የተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም የምርጫ ፅ/ቤቱ የተፈረመበትን ቅፅ በ5 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ዋና ፅ/ቤት መድረሱን ያረጋግጣሉ4.የልዩ ምርጫ ክልል ተወካይ የሆነ የምክር ቤት አባል የይውረድልን ማመልከቻ የሚያቀርቡ የልዩ ምርጫ ክልሉን መራጮች ቁጥር ብሎም ቦርዱ ለዚሁ ጉዳይ በሚያዘጋጀው ቅፅ ላይ ፊርማ የሚያኖሩ ግለሰቦችን ቁጥር በተመለከተ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ በየጊዜው በመስጠት ይህንኑ መራጩ ህዝብ በይፋ እንዲያውቀው ያደርጋል።

**አንቀፅ 16. <u>የይውረድልን ጥያቄ ስለሚቀርብበት ጊዜ</u>**

1. የይውረድልን ጥያቄ በምክር ቤቱ የስራ ዘመን የመጀመሪያ አመት እንዲሁም የመጨረሻ አመት የቀረበ ከሆነ እንደአግባብነቱ በቦርዱ ዋና ጽ/ቤት ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ውድቅ መደረግ አለበት።
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የይውረድልን ማመልከቻው ላይ የተመለከተውን ምክንያት ክብደት መሰረት በማድረግ ቦርዱ በልዩ ሁኔታ ጥያቄው በምክር ቤት የመጀመሪያ አመት ላይም እንዲቀርብ ሊፈቅድ ይችላል።

**አንቀፅ 17. <u>ፊርማ መስጠት ስለሚችሉ ሰዎች</u>**

የይውረድልን ማመልከቻ አቅራቢዎቹ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 14 ንዑስ ቁጥር 1 መሰረት ፊርማ የሚሰበስቡት

ሀ/ የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ተወዳድሮ በነበረበት የምርጫ ክልል በመራጭነት ተመዘግበው የመረጡእናና፤

ለ/ የምክር ቤት አባሉ ተወዳደሮ በነበረበት የምርጫ ክልል የነበረው ምርጫ ከተደረገ በኋላ የመምረጥ መብታቸው በህግ ወይም በፍርድ ውሳኔ መሰረት ያልተገፈፈ መራጮች ብቻ ነው።

**አንቀፅ 18. ማስፈረሚያ ቅፁ ሊይዛቸው የሚገቡ መረጃዎች**

የይውረድልን ማመልከቻ በቦርዱ ዋና ጽ/ቤት ተቀባይነት አግኝቶ መሟላት የሚገባው የፊርማ ቁጥር በማመልከቻ አቅራቢዎቹ አማካይነት ተሰብስቦ እንዲቀርብ ቦርዱ ውሳኔ ከሰጠ ቦርዱ ከዋና ጽ/ቤት ለሚያሰማራቸው አስፈፃሚዎች የሚሰጠው ወይም ለምርጫ ጽ/ቤት የሚላከው የማስፈረሚያ ቅፅ ተመዝግበው የመረጡ መራጮችን ፊርማ አካቶ ከዋና ጽ/ቤት ለተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም ለምርጫ ፅ/ቤት ሲቀርብ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ መሆን ይገባዋል፡-

ሀ/ የፈራሚውን ሙሉ ስም

ለ/ እድሜ

ሐ/ ፆታ

መ/ አድራሻ /ወረዳ፣ቀበሌ፣የቤት ቁጥር ወይም የመኖሪያ አድራሻው ልዩ መጠሪያ/

ሠ/ ቀድሞ በነበረው ምርጫ ማንነት በምስክር ያልተረጋገጠ ከሆነ፤ ማንነቱን ለማረጋገጥ ያቀረበው ሰነድ/ የነዋሪነት መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ መንጃ ፈቃድ፣ የተማሪ መታወቂያ፣ ሰራተኛ መታወቂያ /

ረ/ የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ተወዳደሮ በነበረበት የምርጫ ክልል ተመዝጋቢ የነበረ መሆኑን

ሰ/ መራጩ መርጦበት የነበረው ምርጫ ጣቢያ ስም (የሚታወቅ ከሆነ)

ሸ/ የመራጩ ፊርማ እና ፊርማው የተሰጠበትን ቀን

ቀ/ ቅፁን ያስሞላው ሰው ሙሉ ስም፣ አድራሻ እና ፊርማ

**አንቀፅ 19. ፊርማን ማረጋገጥና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት**

1. በአንቀፅ 14 መሰረት የቀረበውን ቅፅ ፊርማ መስጠት በሚችሉ የምርጫ ክልሉ ነዋሪዎች የተፈረመ መሆኑን እንዲሁም ቅፁ ላይ የሰፈሩት መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የይውረድልን ማመልከቻ ያቀረቡት አመልካቾች የተፈረመበትን ቅፅ ከዋና ፅ/ቤት ለተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም ለምርጫ ፅ/ቤት ሲያቀርቡ ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ ቃለ መሀላ መቀበያ ፎርም ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል።
2. የማጣራት ስራውን ለማከናወን እንዳይቻል የአንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች መዝገብ የጠፋ፣ የተበላሸና የማጣራት ስራውን ለማከናወን በማያስችልበት ሁኔታ የሚገኝ ከሆነ ቦርዱ የተመዘገቡ መራጮችን የመለየት ስራውን በአግባቡ የሚያከናውንበት ውጤታማ ዘዴ ነድፎ በሚገባ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል። ዘዴው በሚነደፍበት ወይም ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት የይውረድልን

ምርጫ ድምፅ መስጠት ሂደቱን በተቀላጠፈና የመራጮችን መብት በሚያስከብር ሁኔታ ማከናወን የሚያስችል መሆኑ ከግምት ሊገባ ይገባል።

3. የቀረበው ቅፅ አግባብነት ባለው ህግ ላይ በተመለከተው መሰረት ቢያንስ በ15000 መራጮች የይውረድልኝ ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ተወዳደሮ በነበረበት የምርጫ ክልል በመራጭነት ተመዘግበው የመረጡ መራጮች አለመፈረሙ በምርመራው ከተረጋገጠ የአመልካቾች ወኪሎች የተጓደለውን ፊርማ አሟልተው በ15 ቀናት ውስጥ እንዲያቀርቡ እንዲያደርግ ቦርዱ ከዋና ፅ/ቤት ለተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም ለምርጫ ፅ/ቤት ያሳውቃል።

4. ፊርማውን በቅፁ ላይ ያላኖረ ግለሰብ የፈረመ በማስመሰል፥ ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀት የሌለን ሰው እንዳለ በማስመሰል ወይም በሌላ የተጭበረበረ መንገድ የቀረበ መረጃ በማናቸውም ሰው በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ቦርዱ በራሱ በሚያደርገው ማጣራት የደረሰበት እንደሆነ፡-

   ሀ/ የተጭበረበረው ፊርማ 5 በመቶ እና ከዚያ በላይ ሆኖ ከተገኘ የቀረበው ማመልከቻ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወዲያውኑ ውድቅ ይደረጋል። ይህንንም ውሳኔ ከዋና ፅ/ቤት በተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም በምርጫ ፅ/ቤት አማካይነት ህዝቡ በይፋ እንዲያውቀው ይደረጋል።

   ለ/ የተጭበረበረው ፊርማ ከ5 በመቶ በታች ሆኖ ከተገኘ ከዋና ፅ/ቤት የተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም የምርጫ ፅ/ቤት በጎደለው ፊርማ ምትክ ትክክለኛ ፊርማ የያዘ ቅፅ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብ በማድረግ በድጋሚ የቀረበውን ቅፅ በአምስት ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ዋና ፅ/ቤት እንዲደርስ ያደርጋል። የቦርዱ ዋና ፅ/ቤትም በድጋሚ የቀረበውን ቅፅ መርምሮ በአስር ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ከዋና ፅ/ቤት ለተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም ለምርጫ ፅ/ቤት በመላክ የምርጫ ክልሉ መራጭ በይፋ እንዲያውቀው ያደርጋል።

   ሐ/ ከማጭበርበር ተግባሩ ጋር ግንኙነት አለው ብሎ ቦርዱ በለየው ግለሰብ/ቦች ላይ የወንጀል ክስ እንዲመሰረት ጉዳዩን ለሚመለከተው ፖሊስ/ አቃቤ ህግ ይመራል።

5. የፊርማ መሰብሰቢያ ቅፁ ህጉ በሚጠይቀው መሰረት ተሟልቶ የቀረበ መሆኑ ከተረጋገጠ ቦርዱ የምርጫ ክልሉን መራጭ ውሳኔ ለማረጋገጥ የይውረድልን ድምፅ አሰጣጥ የሚደረግበትን የጊዜ ሰሌዳ ከማመልከቻ አቅራቢዎች፣የይውረድልኝ ጥያቄ ከቀረበበት የምክር ቤት አባል እና ከወከለው የፖለቲካ ፓርቲ እንዲሁም በምርጫ ክልሉ ከሚገኙ ባለድርሻዎች ጋር በመመካከር ወስኖ ይህንኑ መራጩ ህዝብ በይፋ እንዲያውቀው ያደርጋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

**ምዕራፍ አራት**

**<u>ይውረድልን ምርጫ አፈፃፀም ሂደት</u>**

**አንቀጽ 20. <u>ስለ ምርጫ ታዛቢዎች እና ጋዜጠኞች</u>**

1. ቦርዱ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ፍቃዳቸው የተሰረዘባቸው እስካልሆኑ ድረስ፤ ተወካዩ ለተወከለበት ምክር ቤት ቀደም ሲል የተደረገውን ምርጫ እንዲታዘቡ ፈቃድ የተሰጣቸው ታዛቢዎች እና ጋዜጠኞች ሌላ ተጨማሪ ፍቃድ ሳያስፈልጋቸው አመኔታ ማጣትን ለመለካት የሚደረገውን የይውረድልን ድምፅ አሰጣጥ የመታዘብ ወይም የመዘገብ መብት አላቸው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ምርጫውን ለመታዘብ የሚፈልጉ አዲስ ታዛቢዎች እና ለመዘገብ የሚፈልጉ ጋዜጠኞች ቢኖሩ ጥያቄያቸውን ለቦርዱ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ ሲሆን፤ ቦርዱም መስፈርት ማሟላታቸውን አረጋግጦ የእውቅና ፈቃድ ይሰጣል።
3. በይውረድልን ምርጫ የሚሳተፉ ታዛቢዎች፣ ዘጋቢ ጋዜጠኞች እና የመገናኛ ብዙሃን ከዋና ፅ/ቤት የሚላኩ አስፈፃሚዎችን፣የምርጫ ጣቢያዎችን፣ የምርጫ ክልሎችን እና ቦርዱን አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች መሰረት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።
4. የይውረድልን ምርጫ ለመታዘብ ፍላጎት ያላቸው ጥያቄ የተነሳበት የምክር ቤት አባል በተወዳደረበት ምርጫ ፍቃድ የተሰጣቸው ታዛቢዎች እና ጋዜጠኞች ፍላጎታቸውን ለቦርዱ እና የይውረድልን ምርጫ ለሚካሄድበት የምርጫ ፅ/ቤት እና ምርጫ ጣቢያ ማሳወቅ አለባቸው።
5. የይውረድልን ምርጫ ላይ በመገኘት የሚታዘቡ የሃገር ውስጥ ታዛቢዎችን ፍቃድ አሰጣጥ፣ አሰራር እና ስነ-ምግባርን በሚደነግጉ መመሪያዎች መሰረት ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።
6. የይውረድልን ምርጫን ለመዘገብ የሚፈልግ ጋዜጠኛና መገናኛ ብዙሃኃን በተመለከተ ቦርዱ ያወጣው የመገናኛ ብዙሃንና ጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ ስነምግባርና አሰራር መመሪያ ቁጥር 2/2012 እንደአግባብነቱ ለዚህ መመሪያም አፈጻጸም ተፈጻሚ ይሆናል።
7. የይውረድልን ምርጫን ለመታዘብ የሚፈልግ የአገር ውስጥ ታዛቢን በተመለከተ ቦርዱ ያወጣው የታዛቢዎች ስነምግባርና አሰራር መመሪያ ቁጥር 5 /2012 ለዚህ መመሪያም አፈጻጸም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 21. <u>የይውረድልን ማመልከቻ አቅራቢዎችና ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ወኪሎች</u>**

1. የይውረድልን ምርጫውን ለመታዘብ ፍላጎት ያላቸው በዋናው ምርጫ ላይ ምክር ቤት አባሉን እንዲወክሉ ከቦርዱ የፓርቲ/እጩ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጣቸው የእጩ ወኪሎችን ዝርዝር በማቅረብ የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ወኪሎቹ በየምርጫ ጣቢያው ተገኝተው ሂደቱን እንዲከታተሉለት ማድረግ ይችላል።
2. ቦርዱ በማንኛውም ጊዜ በምርጫ ጣቢያው የሚገኙትን ፈቃድ የተሰጣቸውን የምክር ቤት አባሉን ወኪሎች ቁጥር ሊገድብ ይችላል።
3. መራጩን ህዝብ በመወከል ማመልከቻ ያቀረቡ አመልካቾችም በየምርጫ ጣቢያው ተገኝተው የአመኔታ እጦት መለኪያ የይውረድልኝ ምርጫውን የሚከታተሉላቸው ወኪሎችን ዝርዝር ከዋና ፅ/ቤት ለተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም ለምርጫ ፅ/ቤት በማቅረብና ፈቃድ እንዲሰጣቸው በማድረግ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን ባሰማሩዋቸው ወኪሎች አማካይነት ሊከታተሉ ይችላሉ።
4. የይውረድልን ምርጫውን እንዲከታተሉ በምክርቤት አባሉ እንዲሁም በማመልከቻ አቅራቢ ተወካዮች በየምርጫ ጣቢያው የተመደቡ ወኪሎች የይውረድልኝ ምርጫ ሂደት ላይ የሚኖራቸውን ቅሬታ በቦርዱ በተዘረጋው የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓትና በተገቢው ህግና መመሪያ መሰረት ማቅረብ ይችላሉ።
5. ቦርዱ ለመደበኛው ምርጫ ያወጣው የእጩ ተወዳዳሪዎች ወኪሎች የፍቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 17/2013 ዓ.ም እንደአግባብነቱ ለይውረድልን ምርጫም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 22. <u>የመራጮች ትምህርት የመስጠት ኃላፊነት</u>**

1. በምርጫ ህጉ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የመራጮች ትምህርት የመስጠት ኃላፊነት በዋነኛነት የቦርዱ ነው።
2. ቦርዱ መራጮች በቂ የይውረድልን ምርጫ ነክ ግንዛቤ የሚያገኙበትን ስልት በመቀየስና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም በምርጫ ክልሉ ለሚኖሩ መራጮች ትምህርት ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል።
3. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ቦርዱ በሚሰጠው የስራ መመሪያ መሰረት ከምርጫ ክልል ፅ/ቤት ጋር በመተባበር የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
4. የይውረድልን ምርጫን አስመልክቶ የሚሰጥ የመራጮች ትምህርት የይውረድልን ምርጫ የተለያዩ ገፅታዎች ላይ ብቻ ያተኮረና በምርጫ ክልሉ ነዋሪ የሆነው መራጭ የይውረድልን ምርጫ ምንነትን በቀላሉ እንዲረዳው በሚያስችል መልኩ ተቀርፆ መሰጠት አለበት። የመራጮች ትምህርት በሚሰጥበት ሂደት በተቻለ መጠን

የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበትን የምክር ቤት አባል የሚመለከቱ ዝርዝር መረጃዎችን አለማካተቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

5. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ለአገር በቀል ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመራጮች ትምህርት እንዲሰጡ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል ። ያለ ፈቃድ የመራጮች ትምህርት በሚሰጥ ማንኛውም ሰው ላይ እንዲሁም ሌሎች ከመራጮች ትምህርት ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች የመራጮች ትምህርት ፈቃድ አሰጣጥ እና የስነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 04/2012 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡

**አንቀጽ 23. <u>የምርጫ ቅስቀሳ ስለማካሄድ</u>**

1. የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል እና መራጨን ህዝብ በመወከል ማመልከቻ ያቀረቡ አመልካቾች የፊርማ ማረጋገጥ ተጠናቆ ቦርዱ የይውረድልን ምርጫ እንዲደረግ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ምርጫው አራት ቀን እስኪቀረው ድረስ የምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ ይችላሉ።
2. የምርጫ ቅስቀሳው ህገ-መንግስቱንና አግባብበት ያላቸው ሌሎች ህጎችን፣ የመራጮችን እና መራጨን በመወከል ማመልከቻ አቅራቢዎችን መብት፣ እንዲሁም የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበትን የምክር ቤት አባል መብት በማክበር በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ መካሄድ አለበት።

**ምዕራፍ አምስት**

**<u>ድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ</u>**

**አንቀጽ 24. <u>በይውረድልን ምርጫ በድምጽ ሰጪነት ስለመሳተፍ</u>**

የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል በተወዳደረበት ምርጫ ክልል ተመዝግቦ የመረጠ ማንኛውም መራጭ በይውረድልን ምርጫ ድምፅ የመስጠት መብት ይኖረዋል።

**አንቀጽ 25. <u>በይውረድልን ምርጫ የድምጽ መስጫ የጊዜ ሰሌዳ</u>**

1. የይውረድልን ምርጫ ድምፅ መስጫ እና ውጤት ይፋ ማድረጊያ ጊዜ ቦርዱ እንዲነሳ ጥያቄ ከቀረበበት የምክር ቤት አባል ወይም ከወከለው የፖለቲካ ፓርቲ እንዲሁም ማመልከቻ ካቀረቡ አካላት እና ሌሎች ባለድርሻዎች ጋር ተመካክሮ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ይወሰናል። በዚሁ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ድምፅ አሰጣጡ እንዲከናወን ያደርጋል።

2. የይውረድልን ምርጫው ድምፅ አሰጣጥ የፊርማ ማረጋገጥ ተጠናቆ ቦርዱ የይውረድልን ምርጫ እንዲደረግ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን በኋላ ባለው 4 /አራት/ ወር ጊዜ ውስጥ መከናወን አለበት።
3. ከላይ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም ቦርዱ የይውረድልን ምርጫ የሚከናወንበትን ጊዜ ከአመልካቾቹ እና እንዲነሳ ጥያቄ ከቀረበበት የምክር ቤት አባል ጋር በመመካከር ለተጨማሪ አንድ ወር ጊዜ ሊያራዝም ይችላል።
4. ጥያቄው የቀረበው በአራተኛ ዓመት የስራ ዘመን ከሆነና በቀጣይ አመት ጠቅላላ ምርጫ የሚከናወን ከሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ይህንኑ ከግምት አስገብቶ ቦርዱ በተቻለ መጠን ቀጣይ ጠቅላላ ምርጫ በሚደረግበት አመት የይውረድልን ምርጫ ላለማከናወን ተገቢውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል።
5. በንዑስ ቁጥር 2 ላይ የተመለከተው ጊዜ እንደተጠበቀ ሆኖ ከጠቅላላ ምርጫ ውጪ በቀጣይ ምርጫ የሚደረግ ከሆነ የይውረድልን ምርጫው ከዚሁ ምርጫ ጋር በአንድነት እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል።
6. ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በተመለከተ ቦርዱ ባወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 26. <u>የይውረድልን ምርጫ አማራጭ ስለማስተዋወቅ</u>**

1. ቦርዱ ለውሳኔ የቀረቡትን ሀሳቦች ለማንኛውም መራጭ ግልጽ በሆነና የመራጮች ሃሳብና ፍላጎትን ገላጭ በሆነ ሁኔታ በጽሁፍ ይቀርጻል (ያስፍራል)።
2. በንዑስ ቁጥር 1 መሰረት የሚቀረፀውና ድምፅ የሚሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ ከዚህ በሚከተለው መልኩ ይቀረፃል

*"--------------------------- የተባለው የ---------------ምክር ቤት አባል ከምክር ቤት አባልነት መነሳትን እደግፋለሁ ወይም አልደግፍም"*

3. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሁለቱን አማራጮች የያዙ ምልክቶች በማዘጋጀት እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባልና የይውረድልኝ ጥያቄ አመልካቾች እንዲመርጡ ያደርጋል፥ ምልክቶቹም በድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ እንዲታተሙ ሊያደርግ ይችላል።
4. የይውረድልን ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል በቀደመው ምርጫ የተጠቀመበትን የምርጫ ምልክት ለመጠቀም ከወሰነ ምልክቱ አልደግፍም የሚለውን አማራጭ እንዲወክል ይደረጋል። የፓርቲ እጩ ከሆነ ፓርቲው ምልክቱ አማራጩን እንዲወክል የፈቀደ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

5. የይውረድልኝ ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ምስል በድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ ይታተማል፡፡

**አንቀጽ 27. ስለ ድምፅ መስጫ ወረቀት**

1. በይውረድልን ምርጫ ድምፅ የሚሰጥበትና ለምርጫ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ የያዘ የድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ መታተም ይኖርበታል፡፡
2. የእያንዳንዱ የድምፅ መስጫ ወረቀት የወረቀት ጥራት፣ ቅርፅ፣ ቀለም፣ ብዛት ወይም ይዘት አስቀድሞ በቦርዱ የሚወሰን ይሆናል፡፡
3. ቦርዱ የቀረቡትን አማራጮች የሚወክሉ ምልክቶችን አዘጋጅቶ እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባልና የይውረድልኝ ጥያቄ አመልካቾች እንዲመርጡ ካደረገ አማራጩን የሚወክሉት ምልክቶች በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ የሚታተሙበትን ቅደም ተከተል በዕጣ ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 28. አንድ ቦታ ብቻ ድምፅ ስለመስጠት**

1. በይውረድልኝ ምርጫ ድምፅ የሚሰጥ መራጭ ቀደም ሲል በመራጭነት በተመዘገበበት በአንድ ቦታ ብቻ ድምፅ መስጠት አለበት፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ በአንድ ጣቢያ ተመዝግበው የነበሩ መራጮች ድምፅ ሰጥተውበት የነበረውን ጣቢያ ከሌላ ጣቢያ ጋር እንዲጣመር የወሰነ እንደሆነ ውሳኔውን ለምርጫ ክልሉ መራጭ ድምፅ አሰጣጡ ከሚከናወንበት ጊዜ 15 ቀን አስቀድሞ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. ከተመዘገበበት ቦታ ውጪ ድምፅ ሲሰጥ የተገኘ ሰው እየሰጠ እጁ ላይ የተያዘው ድምጽ በድምጽ ቆጣሪዎች ዋጋ አልባ ይደረጋል፡፡ አግባብ ባለው ሕግም ይጠየቃል፡፡

**አንቀጽ 29. የምርጫ ጣቢያዎች ደህንነት**

1. የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ መስጫ ዕለት ከመድረሱ በፊት ደህንነታቸውና ጥበቃቸው አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ በምርጫ አስፈጻሚዎች መዘጋጀት አለባቸው፡፡
2. እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ የድምጽ መስጫ ጣቢያውን ደህንነት የማስጠበቅ ሀላፊነት አለበት፡፡
3. የምርጫ ጣቢያዎች ደህንነት ቦርዱ ባወጣው የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋማት ጸጥታ አስከባሪዎች የአሰራርና የሥነ ምግባር መመሪያ መሰረት እንዲጠበቅ ይደረጋል፡፡

4. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ የድምጽ መስጫ ጣቢያውንና የአካባቢውን ፀጥታና ደህንነት የሚያስከብሩ የፖሊስ ወይም የፀጥታ አስከባሪዎች ቦርዱ ባወጣው የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋማት ጸጥታ አስከባሪዎች የአሰራርና የሥነ ምግባር መመሪያ መሰረት እንዲመደቡለት ያደርጋል።
5. የድምጽ መስጫ ቀን የድምጽ መስጫ ጣቢያው ከመከፈቱም ሆነ ድምጽ አሰጣጡ አልቆ ከተዘጋ በኃላ ከይውረድልን ምርጫ አስፈጻሚዎች፣ ከታዛቢዎች፣ ወኪሎችና፣ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም።
6. ቦርዱ ያወጣቸው ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ::
7. ቦርዱ ያወጣው የምርጫ የጸጥታ አስከባሪዎች የሥነ ምግባርና የአሰራር መመሪያ ለይውረድልኝ ምርጫ አፈጻጸምም እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀጽ 30. <u>የድምጽ መስጫ ሰዓት</u>**

1. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የይውረድልን ምርጫ የድምጽ መስጫ ሰዓት ከማለዳው 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት ድረስ ነው።
2. ቦርዱ የድምጽ መስጫ ሰዓቱን በተለየ ሁኔታ የወሰነ እንደሆነ የተወሰነውን የድምጽ መስጫ ሰዓት ድምጽ ሰጪዎች በይፋ እንዲያውቁት ይደረጋል።
3. ከላይ በንዑስ አንቀጾቹ የተጠቀሰው ቢኖርም ቦርዱ የምርጫውን ነፃና ፍትሀዊነት ይበልጥ ያረጋግጣል ብሎ ካመነ የድምፅ መስጫ ሰዓቱ እንዲራዘም ሊያደርግ ይችላል።

**አንቀጽ 31. <u>አግባብነት ያላቸው ህጎች ተፈፃሚነት</u>**

አዋጁና ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጥራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ቁጥር_14_/2013 ድንጋጌዎች በይውረድልን ምርጫ ድምፅ አሰጣጥ፥ ቆጠራ እና ውጤት አገላለፅ ሂደትን በሚመለከትም እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ የሚሆኑ ይሆናል።

**አንቀፅ 32. <u>የምርጫ ውጤቱ ዋጋ አልባነት መለኪያ</u>**

1. አሸናፊውን ለመለየት ከየምርጫ ጣቢያው የተሰበሰበውን ውጤት ከማዳመሩ በፊት እንዳግባብነቱ ከቦርዱ ዋና ፅ/ቤት የተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም የምርጫ ፅ/ቤቱ በምርጫ ክልሉ ድምፅ የሰጡ መራጮች

አጠቃላይ ቁጥር እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ቀደም ሲል በተደረገው ምርጫ በተወዳደረበት ምርጫ ክልል ተመዝግበው ከመረጡ አጠቃላይ መራጮች 75 በመቶ እና ከዚያ በላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. በምርጫ ክልሉ የተሰጠው ድምፅ እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ቀደም ሲል በተደረገው ምርጫ በተወዳደረበት ምርጫ ክልል ተመዝግበው ከመረጡ አጠቃላይ መራጮች ውስጥ ከ75 በመቶ በታች የሆኑት ብቻ ድምፅ የሰጡ ከሆነ እንዳግባብነቱ ከዋና ፅ/ቤት የተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም የምርጫ ፅ/ቤቱ ይህንኑ በማረጋገጥና ዋጋ አልባ ይደረግ ከሚል የውሳኔ ሀሳብ ጋር ማዳመሩን ሳያከናውን ለመጨረሻ ውሳኔ ለቦርዱ ዋና ፅ/ቤት ይልካል፡፡
3. የቦርዱ ዋና ፅ/ቤት በንዑስ ቁጥር 2 መሰረት የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ከመረመረ በኋላ መራጮች የሰጡት አጠቃላይ ድምፅ ውድቅ እንዲደረግ ወዲያውኑ ይወስናል ወይም በመራጮች ቁጥር ላይ ድጋሚ ቆጠራ ተደርጎ ውጤቱ እንዲቀርብለት ሊያዝና በዚሁ ላይ መሰረት በማድረግ የአጠቃላይ ውጤቱን ድምፅ ዋጋ አልባ መሆን አለመሆን ይወስናል ፡፡
4. በድጋሚ ቆጠራ ድምፅ የሰጡ አጠቃላይ መራጮች ቁጥር ከተመዘገቡ መራጮች ቁጥር 75 በመቶ እና ከዚያ በላይ መሆኑ ከተረጋገጠ እንደአግባብነቱ ከዋና ፅ/ቤት የተላኩት አስፈፃሚዎች ወይም የምርጫ ፅ/ቤቱ የድምፅ ማዳመሩን አጠናቆ ውጤቱን ለምርጫ ክልሉ መራጭ ያሳውቃል እንዲሁም ውጤቱ ይፋ እንዲደረግ ለቦርዱ ዋና ፅ/ቤት ይልካል፡፡

## አንቀፅ 33. <u>አሸናፊውን ስለመለየት</u>

1. 2/3ኛና ከዚያ በላይ ቁጥር ያለው የመራጮች ድምፅ የምክር ቤት አባሉ መነሳት አለበት የሚለውን አማራጭ የደገፈ እንደሆነ የምክር ቤት አባሉ መነሳት በይፋ ተወስኖ ውሳኔውን የምርጫ ክልሉ ህዝብ በይፋ እንዲያውቀው ውጤቱ በፅ/ቤቱ ይለጠፋል፡፡ የምክር ቤት አባሉ በምርጫ ቦርድ ተሰጥቶት የነበረው የአሸናፊነት መታወቂያ ወዲያውኑ እንዲመክን ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 መሰረት መራጩ ህዝብ ቢያንስ በ2/3ኛ ድምፅ የምክር ቤት አባሉ መነሳት አለበት የሚለውን አማራጭ ካልመረጠ አባልነቱ የሚቀጥል ይሆናል፡፡
3. ቦርዱ ያወጣው የድጋሚ ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ እና ሌሎች መመሪያዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀፅ 34. <u>የይውረድልን ጥያቄ በድምፅ ብልጫ ውድቅ ከተደረገ ጥያቄ ድጋሚ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ</u>**

መራጩ የምክር ቤት አባሉን የይውረድልን ጥያቄ 2/3ኛና ከዚያ በላይ በሆነ ድምፅ ውድቅ ያደረገው እንደሆነ በተመሳሳይ ምክንያት የምክር ቤት አባሉን የሚመለከት ሌላ የይውረድልን ጥያቄ በማናቸውም የምክር ቤቱ የስራ ዘመን በድጋሚ ማቅረብ አይቻልም።

**አንቀፅ 35. <u>በቦርዱ ስለሚሰጥ ይፋዊ መግለጫ</u>**

1. የይውረድልን ምርጫው ሂደት ተጠናቆ አስፈላጊ መረጃዎች ከምርጫ ፅ/ቤት ተሰብስበው ከተረጋገጡ በኋላ ቦርዱ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ ይፋዊ መግለጫ ያወጣል። መግለጫውም የሚከለቱትን ጉዳዮች ይይዛል፡-

    ሀ. እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት የምክር ቤት አባል ቀደም ሲል አሸናፊ በነበረበት ምርጫ በምርጫ ክልሉ ተመዝግበው የመረጡ መራጮች ቁጥር፣

    ለ. በይውረድልኝ ምርጫው ድምፅ የሰጡ መራጮች ብዛት፣

    ሐ. በይውረድልኝ ምርጫው ድምፅ የሰጡና ያልሰጡ ተመዝጋቢ መራጮች በመቶኛ፣

    መ. ለምርጫ የቀረቡት የውሳኔ ሃሳቦች፣

    ሠ. የተመረጠው ውሳኔ ሃሳብ፣

    ረ. ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ጥቅም ላይ ያልዋሉና ከጥቅም ውጭ የሆኑ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛት፣

    ሰ. እያንዳንዱ አማራጭ ሃሳብ በየምርጫ ጣቢያው እንዲሁም አጠቃላይ በምርጫ ክልሉ ያገኘው የድምፅ ውጤት፣

    ሸ. የይውረድልኝ ጥያቄው በመራጩ አብላጫ ድምፅ ድጋፍ ያገኘ ከሆነ በቀጣይ የሟሟያ ምርጫ የሚደረግ መሆኑን።

## ምዕራፍ ስድስት

## ስለ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት እና በድምፅ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ ሂደት ስለሚቀርብ ቅሬታ አፈታት

**አንቀፅ 36. በድምፅ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ ሂደት ስለሚቀርብ ቅሬታ**

1. በድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራ፣ ማዳመር እና ውጤት አገላለፅ ሂደት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 በተዘረዘረው እንዲሁም ቦርዱ ባወጣው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 10/2013 ዓ.ም. እና የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጥራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ቁጥር 14/2013 መሰረት ውሣኔ ያገኛሉ፡፡
2. የይውረድልኝ ምርጫ አስፈጻሚ ሀላፊዎች ለጽሕፈት ቤታቸው የቀረቡ ቅሬታዎችና ለቅሬታዎቹ የተሰጡ ውሣኔዎችን ዋና ቅጂ እና የፅሑፍ ማስረጃዎችን ፋይል አድርገው መያዝ አለባቸው።

## ምዕራፍ ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 37. በጀት**

ቦርዱ ለይውረድልኝ ምርጫ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን በጀት ከመንግስት ያስፈቅዳል።

**አንቀጽ 38. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ወይም አካል የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የመተባበር ግዴታ አለበት፡

**አንቀጽ 39. ስለቅጣት**

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ከጣሰ ወይም ሆን ብሎ የይውረድልኝ ጥያቄውን ማናቸውም ሂደት የሚያሰናክል ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ይጠየቃል፡፡

**አንቀጽ 40. ተጨማሪ ህጎችና መመሪያዎች**

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል ቦርዱ ያወጣቸው የተለያዩ የምርጫ ማስፈጸሚያ መመሪያዎች እንደአግባብነታቸው በይውረድልኝ ምርጫ አፈጻጸም ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 41. <u>ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎችና አሰራሮች</u>**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

**አንቀጽ 42. <u>የመመሪያ ተፈፃሚነት</u>**

ይህ መመሪያ ከመፅናቱ በፊት የቀረቡ የይውረድልኝ ጥያቄዎች በዚህ መመሪያ መሰረት የሚፈፀሙ ይሆናል።

**አንቀጽ 43. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከጸደቀበት ከጥቅምት 19 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ**

**ጥቅምት 19 ቀን 2016 ዓ.ም.**

**<u>ውብሸት አየለ</u>**

**<u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ</u>**